# SEATTLE DEPARTMENT OF NEIGHBORHOODS

# COMMUNITY LIAISONS (የማህበረሰብ አገናኞች)

***ከተማ እንደ መሆናችን መጠን፣ በመኖሪያ ሰፈሮቻችን ውስጥ ያሉትን ሰዎች የሚወክሉ የዘሮች፣ የባህሎች፣ የጾታ መለዮዎች፣ የጾታዊ አዝማሚያዎችንና የማህበራዊ-ኢኮኖሚ ደረጃዎች ስብጥርን ዋጋ እንሰጠዋለን። ሁሉም ድምጽ ተሰሚነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ፣ ከተማው የሚያደርጋቸው የቅስቀሳና የተሳትፎ ጥረቶች ሁሉንም በአክብሮት ዓይን የሚያዩና ተገቢነት ያላቸው መሆናቸው አስፈላጊ ነው።***




## *የፕሮግራም ዝርዝር መረጃዎች*

Community Liaisons (የማህበረሰቡ አገናኞች)፣ ገለልተኛ ተኮናታሪዎች ሲሆኑ፣ ወትሮ ተገቢ ውክልና በሌላቸው ማህበረሰቦች ውስጥ፣ ማለትም ነጭ ያልሆኑ ማህበረሰቦችን፣ እንግሊዝኛ አጣርተው የማይናገሩ ማህበረሰቦችን፣ ኢሚግራንት እና ስደተኛዎችን፣ የ LGBTQ ማህበረሰብን፣ አካለ ስንኩላንን፣ አረጋውያንን፣ እና የጎዳና ተዳዳሪዎችን ጨምሮ፣ ጉዳዮችን የማከናወን ሞያ ያላቸው ናቸው።




የማህበረስብ አገናኞች ከአንድ በላይ ባህል ያላቸውና ከአንድ ቋንቋ በላይ መናገር የሚችሉ “ድልድይ-ገንቢ” ባለሞያዎች ናቸው። ስራቸው የሚካሄደው በባህላዊ ልዩ የአሰራር መንገድ ሲሆን፣ ተሳታፊዎች የከተማውን የጉዳይ አፈጻጸም ሂደቶች በሚከታተሉበት ጊዜ እንዲረጋጉና ግራ እንዳይጋቡ ያደርጋሉ። አገናኞቻችን የሚከተሉትን ጨምሮ የተለያዩ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፥

- ጥራቱን የጠበቀ የማስተርጎም አገልግሎት
- ፍትሃዊና ሚዛናዊ መስተንግዶ (በትውልድ ቋንቋ)
- በአንድ ጊዜ የቃል ማስተርጎም አገልግሎት
- ከተማው በሚያዘጋጃቸው ፕሮግራሞች ላይ ለመራጮች ድጋፍ
- ስለ ባህላዊ ነክ አሳሳቢ ጉዳዮችና መሰናክሎች ገንቢ ሃሳቦችና የባለሞያዊ ምክር
- ተሳታፊዎች ስለ ሰጡዋቸው ገንቢ ሃሳቦችና አሳሳቢ ጉዳዮች ትክክለኛ የሆኑ ሰነዶችና ዘገባዎች
- ታላላቅ ከተማዎች ከሚያስተናግዷቸው ስብሰባዎች ጋር ተጓዳኝ የሆኑ ማህበረሰብ ዎርክሾፖችና ዝግጅቶች



Seattle Neighborhoods

**LEADERSHIP DEVELOPMENT**

SEATTLE DEPARTMENT OF NEIGHBORHOODS

# COMMUNITY LIAISONS (የማህበረሰብ አገናኞች)

ይህ ፕሮግራም የከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተሟላ አገልግሎት ካላገኙ ማህበረሰቦች ጋር በእውነተኛና ባህልን በሚያከብሩ መንገዶች እንዲያሳትፉ አጠቃላይ ስልቶችን ያቀርብላቸዋል። Community Liaisons፣ በማህበረሰብ ፍላጎቶችና በእያንዳንዱ የከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የቅስቀሳ ግቦች መሰረት፣ ከግለሰቦች፣ ከድርጅቶች፣ ትንንሽ ንግድ ድርጅቶችና ከሌሎች ጋራ ይገናኛሉ። መረጃ ያካፍላሉ፣ ቡድኖችን ከአገልግሎቶች ጋራ ያገናኛሉ፣ ችግሮች ሲነሱ መልስ ይሰጣሉ፣ እንዲሁም ቴክኒካዊ እርዳታ ያቀርባሉ። በየቤቱ እየሄዱ ቅስቀሳ ያደርጋሉ እንዲሁም በአንድ ትኩረት በሚደረግበት የቡድን ዓይነት ዝግጅት የከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በቀጥታ ገንቢ ሃሳብ እንዲያገኙ በምክር ክፍለ ግዜዎች ላይ ይሳተፋሉ። ለማህበረሰቡና ለከተማው እንደ እውነተኛ አገናኝ ሆነው ያገለግላሉ።




## *COMMUNITY LIAISONS INSTITUTE*

የእኛ Community Liaisons ሞያዊ እድገትና ብልጽግና በጣም አስፈላጊ ነው። በእኛ የ Community Liaisons Institute በኩል፣ አገናኞቻችንን ለማጠናከር፣ ለማስላትና አዳዲስ ልምዶችን እንዲገነቡ የሚያስችሏቸውን ነጻ ወርሐዊ ስልጠናዎችን እንሰጣለን። እንደ ገለልተኛ ተኮናታሪ ስለ ታክስ አሞላል፣ በአደባባይ ንግግር ስለማድረግ፣ የቃል ማስተርጎም መልካም ተግባሮች፣ ከተማው ስለሚሰጣቸው አገልግሎቶች አጠቃላይ መግለጫ፣ ትኩረት ለሚደረግባቸው ቡድኖች መስተንግዶ፣ እንዲሁም ሌሎችን ጨምሮ ስልጠናዎችን እናደርጋለን።

## *COMMUNITY CONVERSATIONS (የማህበረሰብ ውይይቶች)*

በማህበረሰብ ውይይታችን በኩል፣ የተሟላ አገልግሎት ካላገኙ ማህበረሰቦች ጋር በተሰበሰቡበት ቦታ ላይ ስለ ከተማው ፕሮግራሞች መረጃዎችን ለመካፈል ማህበረሰብን መሠረት ካደረጉ ድርጅቶች ጋር በአባሪነት እንሠራለን። እነዚህ ፕሮግራሞች፣ ለእያንዳንዱ ማህበረሰብ ተብለው ስለተዘጋጁ አርእስቶች ገለጻ ማድረግና፣ ስለ ከተማው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አገልግሎቶች መረጃ የሚሰጡ የመረጃ ጣቢያዎችን ያካተቱ ይሆናሉ። የእኛ የ Community Liaisons፣ ተሳታፊዎች የተለያዩ መርጃ ምንጮችን ፈልገው ማግኘት እንዲችሉ ይረዳሉ፣ እንዲሁም በተለያዩ ቋንቋዎች የቃል እና/ወይም የጽሑፍ ትርጉም አገልግሎቶች ድጋፍ ያቀርባሉ።

ተገቢ ውክልና ያላገኙ ማህበረሰቦችን የሚያገለግሉና ማህበረሰብን መሠረት ያደረጉ ድርጅት ሆነው ሊያስተናግዱን ፍላጎት ካለዎት፣ በ DON_Liaison@seattle.gov ኢሜይል ይላኩ።



*የመገናኛ መረጃ*


**Linet Madeja**

**206-233-0070**

**linet.madeja@seattle.gov**

**seattle.gov/neighborhoods/community-liaisons**